# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ
# ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት
# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት
## በቡና ምርምር ፕሮጀክት ላይ የተደረገ የክዋኔ
## ኦዲት ሪፖርት

ሐምሌ 2002 ዓ.ም.

# ማውጫ


ክፍል አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ........ 3

የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 4!

የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባራት ........ 4

የኦዲቱ ዓላማ ........ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና የመመዘኛ መስፈርቶች(Audit Issues and Evaluation Criteria) ........ 6

የኦዲት ወሠንና ስልት (ዘዴ) ........ 7

ክፍል ሁለት ........ 8

የኦዲት ግኝቶች ........ 8

የፕሮጀክት አሰራር ሂደትን በሚመለከት የስራ መመሪያ (Guideline) ስለመዘጋጀቱ ፡- ........ 8

ለፕሮጀክት ሥራዎች የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂክ ዕቅድ በተመለከተ ........ 9

የምርምር ፕሮጀክቶች ሐሳብ የማመንጨት ሂደት ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ስለመሆኑ ........ 9

የፕሮጀክቱ ዓመታዊ እቅድ ሊሳካ በሚችል መልኩ የሚዘጋጅ መሆኑን በተመለከተ ........ 9

የፕሮጀክት መዋቅርን በተመለከተ ........ 10

የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾች አዘገጃጀትን በተመለከተ ........ 11

የቡና ምርምር ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መጠናቀቁን በተመለከተ ........ 12

የፕሮጀክቱ ሥራ ኦዲት የተደረገ መሆኑን በተመለከተ ........ 13

በፕሮጀክቱ ሥራ ላይ የክትትልና ግምገማ ሥራ የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ ........ 14

በግብርና ምርምር ስራ ላይ ከተሰማሩ የክልል መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ ........ 15

በምርምር ስራው ላይ ያሉ ባለድርሻዎችን የመለየት ስራ የሚሰራ ስለመሆኑ ........ 16

ክፍል ሦስት ........ 18

የማሻሻያ ሐሳቦች ........ 18

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ግብርና ከ84.45% በላይ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደርበት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ሲሆን የዚሁ ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት ከሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ ዝቅተኛ መሆን ከሚጠቀሱት በርካታ ችግሮች መካከል የቴክኖሎጂ መሠረቱ ዝቅተኛ መሆን አንዱና ዋነኛው ሆኖ ይገኛል፡፡
2. በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ሥራ የተጀመረው በ1930ዎቹ ሲሆን፣ ምርምር በአንፃራዊነት በተጠናከረና በመደበኛነት በ1940ዎቹ በጅማና አምቦ የቴክኒክ ት/ቤቶችና በዓለማያ ኮሌጅ በኋላም በደብረዘይት ግብርና ምርምር ማዕከል በመክፈት ተደራጅቶ ተጀምሯል፡፡ በዚህ ወቅት ምርምር፣ ትምህርትና ሥርፀት በጥምረት እንዲካሄድ ሆኖ የተደራጀ ሲሆን በኋላ የግብርና ሚኒስቴር የሥርፀቱን ሥራ እንዲረከብ ተደረገ፡፡ የምርምር ሥራም ራሱን የቻለ አመራር እንዲኖረው ታስቦ በ1958 ዓ.ም. የግብርና ምርምር በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲደራጅ በአንድ ተቋም ሥር ይካሄዱ የነበሩት የግብርና ትምህርት እና የኤክስቴንሽን ምርምር በተለያዩ ድርጅቶች እንዲካሄዱ ተደርጓል፡፡ የግብርና ምርምርን በአገር አቀፍ ደረጃ በማስተባበርና በተለያዩ ሥነ-ምሕዳሮች የምርምር ማዕከላትን በማቋቋም ምርምር እንዲሰራ የእርሻ ምርምር ኢንስቲትዩት ተቋቁሞ በተወሰኑ የምርምር ዘርፎች የምርምር ሥራ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡
3. ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ልማትና ለሕዝቦቿ ማህበራዊ ዕድገት መሠረት የሆነውን ግብርናን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የሚያገለግሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለማፍለቅ፣ አገር በቀል የሆኑትን ለማበልጸግና ከውጭ የተገኙትን /የሚገኙትን/ ከአገሪቱ የግብርና ልማት ፍላጎት ጋር ለማጣጣም ምርምር ወሳኝነት ያለው የልማት እንቅስቃሴ ነው፡፡ የግብርና ምርምር ለአገሪቱ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነት በቀጣይነት ማደግ አስተዋጽኦ የሚኖረው ወጥነት ባለው ሥርዓትና በቅንጅት ሲራመድ መሆኑ እሙን ነው፡፡

4. የግብርናው ዘርፍ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት የጀርባ አጥንት ቢሆንም የቴክኖሎጂ መሰረቱ ዝቅተኛ መሆን በዘርፉ ሊመጣ የሚፈለገውን ለውጥ ማስገኘት እንዳልቻለ በኢንስቲትዩቱ በተገኙ የተለያዩ ጽሁፎች ላይ ተገልጿል፡፡ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ የማበልፀግና የማላመድ ኃላፊነት ተሰጥቶት የግብርና ምርምር ድርጅት በ1989 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 79 ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተጠሪ ሆኖ ተቋቁሞ የነበረ ሲሆን ይህ አዋጅ ተሻሽሎ በ1997 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 382 የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ እንዲሆን ተደርጎ ተቋቁሟል፡፡

5. ኢንስቲትዩቱ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ የአገሪቱን ልማት ለማፋጠን ፋይዳ ያላቸውን የምርምር ሥራዎችና ውጤቶች ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡ እ.ኤ.አ. ከ1970 እስከ 2005 ባለው ጊዜ ውስጥ 435 ያህል የተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎች አስመዝግቧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ 49 የተሻሻሉ የእንስሳት አስተዳደር ቴክኖሎጂዎችን፣ 45 የተፈጥሮ ሐብት አስተዳደር፣ 9 የእርሻ ምህንድስና እንዲሁም 5 የደን ልማት ቴክኖሎጂዎች አስመዝግቧል፡፡

6. ሌሎች የምርምር ውጤቶች ለመጥቀስ ያህልም፣ አካላ የተባለውን የጥጥ ዝርያ በማስተዋወቅ ጥጥን ለሚያጠፉ ተባዮች ይረጭ የነበረውን የፀረ-ተባይ መድሐኒት መቀነስ፣ ቀደም ላሉት ዘመናት ለኢትዮጵያ ዋና የውጭ ንግድ ሸቀጥ የነበረውን ነጭ ወርቅ የተባለውን የነጭ ቦሎቄ ዝርያን ለአምራቾችና ነጋዴዎች ማስተዋወቅ፣ በምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ተከስቶ የነበረውን የቡና ግንድ አድርቅ በሽታን የሚቋቋሙ ዝርያዎችን መለየት እና ማስተዋወቅ፣ ለቢራ ኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንዲያድኑ ያስቻላቸውን የብቅል ገብስ ማስተዋወቅ፣ ጥቁር አፈር መልሶ እንዲያንሰራራና ምርታማ እንዲሆን የሚያደርግ ቴክኖሎጂን ማፍለቅ ከብዙዎቹ መካከል ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ ኢንስቲትዩቱ በአሁኑ ወቅት በ26 የተለያዩ የምርምር ፕሮግራሞች የታቀፉ 70 የምርምር ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

7. በኢንስቲትዩቱ ከሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል የቡና ምርምር ፕሮጀክት አንዱ ነው፡፡ ቡና አገሪቱ ከምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ውስጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 65% ይሸፍን የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት አገሪቱ እንደ አበባ፣ ወርቅ፣ ቆዳና ሌጦ የመሳሠሉትን ምርቶች ወደ ውጭ መላክ ከጀመረች በኋላም

እስከ 35% የሚሆነውን የውጭ ምንዛሪ በመሸፈን ለአገሪቷ ኢኮኖሚ አይነተኛ አስተዋጽኦ ያደጋል፡፡

8. በአገሪቱ የተለያዩ የቡና ዝርያዎች እና ለቡና አመቺ የሆኑ ሁኔታዎች ቢኖሩም በባህላዊ የአስተራረስ ዘዴ፣ በቡና በሽታዎች፣ በተባዮችና በምርጥ ዘር እጥረት ምክንያት አጠቃላይ የቡና ምርት እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም አገሪቷ በአሁኑ ጊዜ በአማካይ በ1 ሄክታር ማግኘት ከነበረባት 15 ኩንታል ምርት ውስጥ የምታገኘው ከ5 ኩንታል ያነሠ ምርት ነው፡፡

9. በኢትዮጵያ የቡና ምርምር የተጀመረው በ1966 ዓ.ም ሲሆን በዚያን ጊዜ የተለያዩ የቡና ዝርያዎችን ከተለያዩ ሀገራት በማምጣት ለማስተዋወቅ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዝርያዎቹን ከሀገሪቱ ሁኔታ ጋር ለማለማመድ በጅማ የግብርናና ሜካኒካል አርት ት/ቤት ከዛም በኋላ በጅማ ብሔራዊ የቡና ምርምር ማዕከል ውስጥ ሙከራ ተደርጓል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የቡና ምርምር በተሻለ ስልት መካሄድ የጀመረው በ1968 የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና የጅማ የምርምር ማዕከል ከተቋቋሙ በኋላ ነው፡፡ ይህንን በመከተልም ተጨማሪ ሰባት ንዑስ የምርምር ማዕከላት ተቋቁመዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሲዳማ፣ ወለጋ፣ ሀሩ፣ ቴፒ፣ ጌራ፣ አጋሮ፣ መቱ፣ አዋዳና ሙጊ የቡና ምርምር እየተካሄደ ይገኛል፡፡

<u>የኢንስቲትዩቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል</u>

10. ኢንስቲትዩቱ በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን ለዋና ዳይሬክተሩ ተጠሪ የሆኑ ሁለት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፣ አንድ የቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ፣ አራት መምሪያዎች፣ አንድ አገልግሎትና አንድ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ሲኖረው፣ ለምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ተጠሪ የሆኑ አምስት የምርምር ዳይሬክቶሬቶች፣ ሶስት መምሪያዎች፣ ሶስት አገልግሎቶች፣ ሁለት የምርምር ማስተባበሪያዎች፣ አንድ የስርዓተ ጾታ ጉዳይ፣ 13 የፌደራል ምርምር ማዕከላት አሉት፡፡

11. በኢንስቲትዩቱ ዋና መ/ቤት፣ በንዑስ ማዕከላትና በሙከራ ጣቢያዎች ኦዲቱ በተደረገበት ወቅት የነበረው የሰው ኃይል ብዛት በድምሩ 3189 ሲሆን ከዚህ ውስጥ የአስተዳደር (Administrative staff)1449፣ የቴክኒክ ዘርፍ (Technical staff)1150 እና በምርምር ዘርፍ (Research staff) 590 ሰራተኞች ናቸው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ

12. የኢንስቲትዩቱ የፋይናንስ ምንጭ ለደመወዝና ለስራ ማስኬጃ የሚሆን ገንዘብ ከመንግሥት የሚመደብለት ሲሆን በዚህም መሠረት በ1999 በጀት ዓመት ለመደበኛ በጀት ብር 8,665,204 እንዲሁም የካፒታል በጀት ብር 57,580,255 ተመድቦ ከዚህ ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ ከመደበኛ በጀት ብር 6,358,455 (73%) እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 56,848,254 (99%) ነው፡፡ ከ1994 - 1998 ዓ.ም. ለሚካሄደው የቡና ምርምር ፕሮጀክት ብር 13,439,923 በጀት ተይዞለታል፡፡ ይህም በኢንስቲትዩቱ ከሚካሄዱት ፕሮጀክቶች ከፍተኛ በጀት የያዘ ፕሮጀክት ነው፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ስልጣንና ተግባራት

13. ኢንስቲትዩቱ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ውስጥ፣

- በአገሪቱ የሣይንስና ቴክኖሎጂ፣ የግብርና ልማትና ምርምር ፖሊሲዎች መሠረት የግብርና የምርምር ስትራተጂ መንደፍና ቅደም ተከተል መወሰን፣ የሥራ ፕሮግራምና ቅድ ማውጣት፣
- የግብርና ምርምር ፖሊሲ አፈጻጸምን መከ ተል፣ አዳዲስና የማሻሻያ የፖሊሲ ሃሳብ ማመንጨት፣
- ከአገሪቱ የልማት ፍላጐት ጋር የሚጣጣም የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለመቅረጽና ለማዘጋጀት የሚያስችል መመሪያ ማውጣት፣
- በግብርና ምርምር ፖሊሲና ስትራተጂ መሠረት የግብርና ምርምር ማከናወን ወይም ንዲከናወን ማድረግ፣
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ጠቃሚነ ቸው የተረጋገጠ የግብርና ምርምር ውጤቶች ተጠቃሚው ክፍል ንዲያውቃቸው፣ በሥራ ላይ ንዲውሉ በፌደራል የግብርና ምርምር ማዕከላትና በተጠቃሚው መካከል ውጤ ማ ቅንጅት ንዲኖር የሚረዳ ሥርዓት መዘርጋት፣
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የህብረተሰቡን የግብርና ውቀት አድማስ ለማስፋፋት ከምርምር የተገኙ ውጤቶችን ለማስተዋወቅ አመች በሆኑ የመገናኛ ዘዴዎች የአህዝቦት ተግባር ማከናወን፣

- በአገር ውስጥና በውጭ አገር የተካሄዱና የሚካሄዱ የግብርና ምርምሮችንና የምርምር ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማከማቸትና ማሰራጨት፣ የመረጃ ቅብብል ሥርዓት መገንባትና መምራት፣
- አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በግብርና ትምህርት፣ ምርምርና ሥርፀት ንዲሁም የምርት ንቅስቃሴ መካከል የርስ በርስ መደጋገፍ ንዲኖር ሁኔ ዎችን ማመቻቸት፣
- በግብርና መስክ የተቋቋሙትን የሙያተኞች ማህበራትን ማበረ ት፣ ንዲሁም ለግብርናው ምርምር በመረጃዎች ልውውጥ አስተዋጽኦ ንዲያደርጉ ሁኔ ዎችን ማመቻቸት፣
- አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የግብርና ምርምር ተቋማትና ደጋፊ ድርጅቶች ንዲሁም ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ብሔራዊ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መመስረት፣ ትብብር ማድረግ፣ ስምምነቶችን መፈራረም ተግባራዊ ማድረግ ወይም ተግባራዊነ ቸውንም መከ ተል፣
- ለክልል የግብርና የምርምር ማዕከላት ተገቢውን የመረጃ አገልግሎት መስጠት ጥያቄም ሲቀርብ አቅሙ በፈቀደ መጠን የቴክኒክ ድጋፍና ገዛ ማድረግ፣
- በፌደራልና በክልል የምርምር ማዕከላት በሚከናወኑ የምርምር ኘሮጀክቶች መካከል አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽና የሀብት መባከን ንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የኘሮጀክት ግምገማ ሥርዓት አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር መዘርጋት፣
- በግብርና ምርምር ላይ የተሰማራ ወይም የሚሰማራ ማንኛውንም ሰው መዝግቦ ዝርዝሩን መያዝ፣

የሚሉ ይገኙበታል፡፡

<u>**የኦዲቱ ዓላማ**</u>

14. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ሥር የሚካሄደው የቡና ምርምር ፕሮጀክት የስራ ሂደት ወጪ ቆጣቢ በሆነ፣ አፈፃፀሙ ብቃት ባለው መንገድ መከናወኑን እና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት ችግሮችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚያስችሉ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለሥራ አመራሩ ለማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች እና የመመዘኛ መስፈርቶች

**(Audit Issues and Evaluative Criteria)**

15. ከላይ የተገለፀውን የኦዲት ዓላማ ለማሳካት 4 የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተመረጡ ሲሆን እነርሱም:-

    i. የቡና የምርምር ኘሮጀክት የምርምር መነሻ ሀሣብ (Project Idea) በትክክል ተነድፎና የአዋጪነት ጥናት (Feasibility Study) የተደረገበት ስለመሆኑ፣ ለቴክኒክ አማካሪ ኮሚቴ ቀርቦ እንዲፀድቅ ስለመደረጉ እና እቅዱም ሊለካ በሚችል መልኩ በዝርዝር መዘጋጀቱን፣
    ii. የቡና ምርምር ኘሮጀክት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ድርጅታዊ መዋቅር የተዘጋጀለት፣ ለእያንዳንዱ የሥራ መደብ ዝርዝር መስፈርቶች የተዘጋጁለትና በሰው ኃይልና ቁሣቁስ (መሣሪያ) እንዲሟላ መደረጉን፣ የመመዝገቢያ ፎርሞች (ቅጾች) የተዘጋጁለት እና ተግባራዊ መሆኑን ማጣራት፣
    iii. የቡና ምርምር ኘሮጀክት በተዘጋጀለት ዕቅድ መሠረት ሥራው መጀመሩን እና መጠናቀቁን፣የሥራ አፈፃፀምና የሀብት አጠቃቀሙ ብቃት ባለውና ቁጠባን ባገናዘበ መልኩ መከናወኑን እንዲሁም አላማውን ስኬታማ ማድረጉን ማጣራት፣
    iv. የቡና ምርምር ኘሮጀክት በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች በየአመቱ እንዲመረመር መደረጉን፣ የክትትልና ግምገማ (Monitoring and Evaluation) ስርዓት ተዘርግቶለት ተግባራዊ መደረጉን፣ ኘሮጀክቱ ለመጠናቀቁም ርክክብ የሚከናወን ስለመሆኑና የትንተና (Analysis) ሥራ ስለመከናወኑ ማጣራት የሚሉ ናቸው፡፡

16. እነዚህን 4 የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ኦዲት ለማድረግ 46 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ ተያይዘዋል፡፡

17. የመመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት  የኢትዮጵያ ግብርናና ምርምር ኢንስቲትዩት ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የኢንስቲትዩቱ የሶስት አመት ስትራቴጂክ ፕላን (ከ1997-1999ዓ.ም)፣ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የሶስት አመት ስትራቴጂክ ፕላን፣ የፕሮጀክት አዘገጃጀትና አሰራር ስርዓት ልምድ (Good project management practice) ናቸው፡፡

## የኦዲት ወሠንና ስልት (ዘዴ)

18. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 68/1989 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ1994 - 1998 የበጀት አመታት የተከናወኑ ተግባራትን ነው፡፡ ይህም ፕሮጀክቱ በአምስት  ዓመት እንዲጠናቀቅ የተያዘውን ዕቅድ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና በጅማ የምርምር ማዕከል መረጃዎችን በመከለስ እና ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የፕሮጀክት አሰራር ሂደትን በሚመለከት የስራ መመሪያ (Guideline) ስለመዘጋጀቱ፡-

19. የቡና ምርምር ፕሮጀክት የሥራ ሂደትን በትክክለኛውና ወጥነት ባለው መንገድ ለማከናወን የሚያስችል የስራ መመሪያ (Manual/guideline) ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

20. ከአገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር ተገናዝበው የሚነደፉ የግብርና ምርምር ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሥራ ሂደት ወጥነት እንዲኖረው የሚያስችል፣ እንደአግባቡም ተዘጋጅተው የሚነደፉ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ያስገኙትን ውጤት ለመገምገምና ተፈጻሚነታቸውንም ለመከታተል የሚያስችል የስራ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ ለቡና ምርምር ኘሮጀክትም ሆነ ለሌሎች የምርምር ኘሮጀክቶች የሥራ መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

21. ይህንንም በተመለከተ በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የፕሮጀክት ፕላን ክትትልና ግምገማ መምሪያ ኃላፊ እንዲሁም የሰብል ምርምር ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ለምርምር ፕሮጀክቶች የስራ መመሪያ እንዳልተዘጋጀ ገልፀዋል፡፡ የጅማ ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ቀድሞ የስራ መመሪያ እንዳልነበረ ነገር ግን አሁን በተደረገው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) የተዘጋጀው ዶክመንት ለወደፊት ለሚከናወኑ የምርምር ኘሮጀክቶች እንደ መመሪያ የሚያገለግል እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በ2000 ዓ.ም በተዘጋጀው የBPR ዶክመንት ላይ ሁለት ዓይነት መመሪያዎች (ቴክኒካል እና ኦፕሬሽናል) እንደሚዘጋጅ ተገልጿል፡፡

22. በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በተደረገው የኦዲት የመውጫ ውይይት ላይ እንደተገለፀው ኘሮጀክቶቹ የተለየ ባህሪ (Unique character) ከሌላቸው ለራሳቸው የተለየ መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው ብለው የማያምኑ መሆናቸውንና ኢንስቲትዩቱ በተለይ BPR ከሠራ በኋላ ከእያንዳንዱ ኘሮጀክት በየዓመቱ የሚጠበቁ ውጤቶችን ንዑስ ግቦት (Milestone) ቀርፆ የሚያስቀምጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የሥራ መመሪያ (Technical manual) በኮሞዲቲ ደረጃ የተዘጋጀ መሆኑ ተገልፆ መረጃው ቀርቧል፡፡

23. ለምርምር ፕሮጀክቶች የስራ መመሪያ ማዘጋጀት ከምርምር ሥራው መነሻ ጀምሮ በየደረጃው የሚከናወኑ ሥራዎች ብቃት ባለው መንገድ በጥራትና በቁጠባ ለማከናወን እና ስኬታማ ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ ለክትትል፣ ለግምገማ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በሥራ መመሪያ በመታገዝ ሥራን አለማከናወኑ በሠራተኞች መለዋወጥ ምክንያት ሊደርስ ለሚችል ወጥነት ለጎደለው አሠራር የሚዳርግ፣ በዕቅድ መሠረት ሥራን ለማከናወን እንቅፋት የሚሆን፣ ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ እና ተጠያቂነትን የማያጠናክር መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

## ለፕሮጀክት ሥራዎች ስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ

24. የቡና ምርምር ፕሮጀክቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ ሊኖረውና፣ በፕሮጀክቱ ስር የተቀረጹ ሥራዎች እና ጥናቶች በዕቅዱ መሰረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡

25. በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ እንደቻልነው ከቡና ምርምር ሥራ በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ሊገኝ የሚፈለገውን ውጤት እና የአሠራር ስልቱን የሚያሳይ የቡና ምርምር የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂክ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን ነው፡፡

26. ይህንንም በተመለከተ ለሰብል ምርምር ዳይሬክተር እና ለፕሮጀክት ፕላን፣ ክትትልና ግምገማ መምሪያ ኃላፊ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በአጠቃላይ ለኢንስቲትዩቱ የተዘጋጀ ስትራቴጂክ ዕቅድ መኖሩን ሆኖም ለእያንዳንዱ የምርምር ፕሮጀክት በተናጠል የተዘጋጀ ስትራቴጂክ ዕቅድ ግን እንደሌለ ገልፀዋል፡፡

27. በኢንስቲትዩቱ በተደረገው የመውጫ ስብሰባ ላይ እንደተገለፀው ቀድሞ የነበረው ስትራቴጂክ ዕቅድ በመ/ቤት ደረጃ የሚዘጋጀው ብቻ እንጂ ለምርምር ፕሮጀክቶች እንዳልነበር ሆኖም በመ/ቤቱ BPR ከተሠራ በኋላ ለየምርምር ኮሞዲቲዎቹ ስትራቴጂክ ዕቅድ እንደሚዘጋጅ ገልፀው መረጃውንም አቅርበዋል፡፡ ለቡና ምርምር ፕሮጀክት ሥራ ስትራቴጂክ ዕቅድ አለመዘጋጀቱ የምርምር ሥራውን ቅርጽ ለማስያዝ ካለማስቻሉም በላይ የምርምር ሥራው በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ለሀገሪቱ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ለማሳየት፣ የፕሮጀክቱ ሥራ በዕቅዱ መሠረት መከናወኑን እና የሚፈለገውን ጥቅም ያስገኘ መሆኑን ለመቆጣጠርና ለመከታተል ካለማስቻሉም በላይ የወደፊት የልማት ስትራቴጂን ለመቀየስ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

## የፕሮጀክቱ ዓመታዊ እቅድ ሊለካ በሚችል መልኩ የሚዘጋጅ መሆኑን በተመለከተ

28. አንድ የምርምር ፕሮጀክት ስራን ማከናወን ከመጀመሩ በፊት በምርምሩ የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች ተለይተውና ተነድፈው ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ሊዘጋጅላቸው

ይገባል፡፡ ዕቅዱም ሊለካ በሚችል መልኩ /በጊዜ፣ በገንዘብ፣ በሰው ኃይል፣ በሚከናወኑ ሥራዎች እና አስፈላጊ ግብዓት…/ ተለይቶ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

29. በኦዲቱ በታየው ከ1994-1998 ዓ.ም ሊሰራ በታቀደው የቡና ምርምር ፕሮጀክት ዶክመንት ላይ ፕሮጀክቱ ለሚያከናውናቸው ዝርዝር ስራዎች እቅድ ሊለካ በሚችል መልኩ የተዘጋጀ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

30. እቅድ ሊለካ በሚችል መልክ የሚዘጋጅ መሆኑ ተጠያቂነትን የሚያጠናክርና ስራው ብቃት ባለው መልኩ እንዲከናወን የሚያደርግ በመሆኑ በኢንስቲትዩቱ ያለው ዓመታዊ የእቅድ አዘገጃጀት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት አሰራር ነው፡፡

## የምርምር ፕሮጀክቶች ሐሳብ የማመንጨት ሂደት ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ ስለመሆኑ

31. በኢንስቲትዩቱ የፕሮጀክቶች ሐሳብ የሚመነጨው (Project Initiation) የምርምር ማዕከላቱ በሚገኙበት አካባቢዎች ባሉ የዞን ወይም የወረዳ የግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ተጠሪዎች ሰብሳቢ በሚሆኑበት የገበሬ ግንኙነት አማካሪ ካውንስል አማካኝነት መሆኑን፣ ይህ ካውንስል የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ይኸውም የምርምር ማዕከላትን፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ እና ገበሬዎችን የሚያቅፍ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በካውንስሉ አማካኝነት ከሚመነጨው የፕሮጀክት ኃሣብ በመነሣት የምርምር ሐሣብ (Project Proposal) እንደሚዘጋጅ ታውቋል፡፡

32. የምርምር ፕሮጀክቶችን ሐሳብ የሚያመነጭ ወይም የሚያሰባስብና የሚያስተባብር ለዚህም ሙሉ ሐላፊነት የተሰጠው አካል ሊኖር ይገባል፡፡ የፕሮጀክት ሐሳብ የሚመነጨው የፕሮጀክቱን ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልክ መሆን ይኖርበታል፡፡ ኢንስቲትዩቱም ይህንን መርህ የሚከተልና ተግባራዊ የሚያደርግ በመሆኑ ሊጠቀስ የሚገባው በጎ አሠራር (Good Practice) ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## የፕሮጀክት መዋቅርን በተመለከተ

33. አንድ የምርምር ፕሮጀክት ግልጽ የሀላፊነትና የተጠሪነት እንዲሁም የስራ ግንኙነት የሚያሳይ የራሱ የሆነ የፀደቀ መዋቅር ሊኖረው ይገባል፡፡ በመዋቅሩ ላይ ለተቀመጠው የስራ መደብ የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛትና የሙያ ዓይነት ተለይቶ እንዲታወቅ መደረግ አለበት፡፡

34. ይሁንና በጅማ የምርምር ማእከል የሚገኘው የቡና ምርምር ፕሮጀክት የራሱ የሆነ ድርጅታዊ መዋቅር የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በምርምር ፕሮጀክቱ ዶክመንት ላይ ለምርምር ስራው የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት እና የሙያ ዓይነት የተገለጸ መሆኑን ከሰነዶች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

35. ይህንንም በተመለከተ ከጅማ ምርምር ማእከል ዳይሬክተር ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እንደተገለጸው የቡና ምርምር ፕሮጀክት የራሱ የሆነ መዋቅር የሌለውና ፕሮጀክቱን የማስፈጸም ኃላፊነት ያለባቸው ባለሙያዎች በሌሎች የምርምር ፕሮጀክቶች ላይ በመሳተፍ የመስራትም ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን አብራርተዋል፡፡

36. በምርምር ፕሮጀክቶች ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች ስራውን በሚፈለገው ደረጃ መስራት እንዲችሉና ግልጽ የሆነ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው አለመደረጉ፣ በተለያዩ ፕሮጀክቶች ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎም ተለይቶ የሚታወቅበት አሰራር አለመኖሩ ተጠያቂነትን ለማጠናከር የስራ ክፍፍልን ለመለየትና የኃላፊነት ድርርቦሽን ለመቀነስ የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡

## የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾች አዘገጃጀትን በተመለከተ

37. የምርምር ፕሮጀክቶቹ የየራሳቸው የበጀት መጠየቂያ፣ ሂሳብና ንብረት አያያዝ፣ ለግዢ፣ የስራ ክንውን ሪፖርት ማቅረቢያ ወ.ዘ.ተ ቅጾች ሊዘጋጁና ቅጾቹም አስፈላጊ መረጃዎችን ያካተቱ እና በአግባቡ ተፈጻሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡

38. ኢንስቲትዩት የበጀት መጠየቂያ፣ ሂሳብና ንብረት አያያዝ፣ የግዢ፣የስራ ክንውን ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾቸ ያለው ሲሆን መሠረታዊ የአሰራር ሂደት ለውጥ (BPR) ከተሰራ በኋላም ተሻሽለው እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ቀድሞ በነበረውም ሆነ አሁን በተዘጋጀው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ የተሰሩ ሥራዎች እና በስራው አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ለማቅረብ የሚያስችል ሆኖ ቢዘጋጅም በሥራው ወቅት የተገኙ ጥሩ ልምዶች (Good Practice) እንዲቀርቡ የሚያስችል ሆኖ አልተዘጋጀም፡፡

39. ይህንንም በተመለከተ ከኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሰብል ምርምር ዳይሬክተር ጋር በተደረገ ቃለምልልስ እንደተገለጸው የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጹ በስራ ላይ የተገኙ ጥሩ ልምዶች እንዲመዘገቡ ስለማይጠይቅ እና ቅጹን በመከተል ሪፖርት የሚቀርብ በመሆኑ ጥሩ ልምዶች የማይመዘገቡ /የማይቀርቡ/ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

40. በስራ ላይ የተገኙ ጥሩ ልምዶችን መዝግቦ መያዝ እና በሪፖርት አካቶ ማቅረብ ወደፊት በሚቀረጹና በሚተገበሩ የፕሮጀክት ስራዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ስለሚኖረው ከወዲሁ ሊታሰብበትና ሊስተካከል ይገባል፡፡

## የቡና ምርምር ፕሮጀክት በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መጠናቀቁን በተመለከተ

41. የምርምር ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስራው መጀመር እና መጠናቀቅ አለበት፡፡

42. የቡና ምርምር ከ1991-93 የመንግስት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ብሄራዊ የቡናና ቅመማ ቅመም ምርምር ፕሮግራም አካል ሆኖ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ ከ1994 ጀምሮ በፕሮጀክት መልክ ተቀርጿል፡፡ የፕሮጀክቱ የስራ ዘመንም ከ1994-98 መሆኑ በፕሮጀክቱ ዝርዝር መግለጫ ላይ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የፕሮጀክቱ ስራ በተያዘለት የሥራ ዘመን ሊጠናቀቅ አለመቻሉን፣ ነገር ግን ተጨማሪ አዳዲስ ተግባራት ታክለውበት የስራ ዘመኑ ለተጨማሪ 5 ዓመታት (ከ1998-2002) የተራዘመ መሆኑን የጅማ ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

43. በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ የመውጫ ስብሰባ ላይ ስራው በተያዘለት የጊዜ ገደብ አለመጠናቀቁን ገልጸዋል፡፡

44. ይሁንና ፕሮጀክቱ ቀደም ብሎ በተያዘለት የሥራ ዘመን መሰረት ያልተጠናቀቀበትን ምክንያት በስራ ዘመኑ ማብቂያም ከዕቅዱ ምን ያህል እንደተጠናቀቀ እና እንዳልተጠናቀቀ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና በጎ የስራ ተሞክሮዎች ተለይተው በሪፖርት እንዲዘጋጁ ባለመደረጉ ዝርዝር ሁኔታውን ለመገንዘብ አላስቻለም፡፡ አንድ ስራ በፕሮጀክት መልክ እንዲቀረጽ መደረጉ የስራውን ወሰን ለመወሰን፣ የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎችን ለመለየት፣ የስራ ማከናወኛ ወጪን እና ጊዜን ለመወሰንና የፕሮጀክቱን ውጤት ለመተለም፣ የክትትልና ግምገማ ስርዓትን ለመንደፍ ወዘተ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት የፕሮጀክቱን ስራዎች እንዲከናወኑ ማድረግና ማሻሻያዎች ማድረግ ካስፈለገም የፕሮጀክት ሰነዱን ባገናዘበ መልኩ የተሰሩና ያልተሰሩ ስራዎች መለየትና አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎች እና ተጨማሪ ስራዎች በግልጽ ተለይተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም ለፕሮጀክቱ ሥራ ማሻሻያ ማድረግና ጊዜ መራዘም ምክንያት በወቅቱ የፕሮጀክቱን ስራ ይከታተሉ የነበሩት የኢንስቲትዩቱ የፕሮጀክት እቅድና ክትትል መምሪያ ኃላፊ ስራ በመልቀቃቸው ሁኔታውን የሚገልጽልንና ማስረጃ የሚያቀርብልን አካል ባለመገኘቱ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ይህም በመሆኑ የፕሮጀክቱ ሥራ በተያዘለት ጊዜ ያልተጠናቀቀበትን ምክንያት ለመለየት እና ሊገጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን በመለየት

ለወደፊት ለሚከናወነው የፕሮጀክት ስራ የመፍትሄ እርምጃዎች ለመንደፍ የማያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

45. የምርምር ፕሮጀክቱ ስራ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ እንዲጠናቀቅ አለመደረጉ የተፈለገው ውጤት በሚፈለገው ጊዜ እንዳይገኝ ከማድረጉም ባሻገር በአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦትና የኢኮኖሚ እድገት እንዲሁም የማህበራዊ ጉዳይ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

## የፕሮጀክቱ ሥራ ኦዲት የተደረገ መሆኑን በተመለከተ

46. የቡና ምርምር ፕሮጀክት ሂሳብ በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች በየዓመቱ ሊመረመር እና የኦዲት ሪፖርቱም ለሚመለከተው አካል ሊቀርብ ይገባል፡፡

47. የጅማ ምርምር ማዕከል አስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ ኘሮጀክቱ እንደ አስፈላጊነቱ በገንዘብ ሚ/ር፣ በኦዲት አገልግሎት ኮርፖሬሽን (የውጭ ኦዲተር)፣ በዋናው መ/ቤት የውስጥ ኦዲት መምሪያ እና በቅርንጫፍ (ማዕከል) የውስጥ ኦዲተሮች አማካኝነት ሂሣቡ ኦዲት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

48. ከኢንስቲትዩቱ የውስጥ ኦዲት መምሪያ ኃላፊ እንዲሁም ከፋይናንስ መምሪያ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ እንደተገለፀው የኦዲት አገልግሎት ኮርፖሬሽን በየዓመቱ በተለያዩ ማዕከላት የሂሣብ ምርመራውን እንደሚያካሂድ እና ሪፖርት እንደሚያቀርብ ገልፀዋል፡፡ በመውጫ ስብሰባው ወቅት እንደተገለጸው ኦዲት የሚደረገው ሁሉንም ኘሮጀክቶች በአንድ ላይ እንጂ እያንዳንዱ ኘሮጀክት በተናጥል አለመሆኑ ተገልጿል፡፡

49. በኦዲት አገልግሎት ኮርፖሬሽን የተዘጋጁ የኦዲት ሪፖርቶችን (ከ1996 እስከ 1998 ዓ.ም ያለውን) ለማየት እንደተቻለው የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትን በየዓመቱ የሂሣብ (Financial) ኦዲት እንደሚያደርግና የምርምር ማዕከላቱን ወይም

የኘሮጀክት ማከናወኛ ስፍራዎቹን እንደ ናሙና በመውሰድ ኦዲት የሚያደርግበት ሁኔታ መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይሁንና በውጭ ኦዲተሮች በቡና ምርምር ኘሮጀክት ላይ የሚቀርቡት የማሻሻያ ሐሣቦች ተግባራዊ ለመሆናቸው ክትትል ያልተደረገባቸው መሆኑን የኢንስቲትዩቱ የኦዲት መምሪያ ኃላፊ ገልፀዋል፡፡ የቡና ምርምር ኘሮጀክት በኢንስቲትዩቱ ከሚከናወኑት የተለያዩ የምርምር ኘሮጀክቶች ከፍተኛውን የገንዘብ ድርሻ የያዘ ሆኖ ሳለ ትኩረት ተሰጥቶት በውስጥ ኦዲት መምሪያው ክትትል ያልተደረገበት መሆኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

**<u>በፕሮጀክቱ ሥራ ላይ የክትትልና ግምገማ ሥራ የሚከናወን መሆኑን በተመለከተ</u>**

50. በፕሮጀክቱ ሥራ ላይ መከናወን ስለሚገባው የክትትልና ግምገማ ሥራ (Monitoring and evaluation) ጋር በተያያዘ ከጅማ ምርምር ማዕከል ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ ለክትትልና ግምገማ ሥራ ዕቅድ ያልተዘጋጀለት፣ የክትትልና ግምገማ ሥራውም በገለልተኛ አካል ሳይሆን የምርምር ሥራውን በሚያከናውነው አካል ብቻ ይካሄድ እንደነበር፣ ነገር ግን በአዲስ አሠራር እንዲተካና የውጭ ሙያተኞች ጭምር በክትትልና ግምገማ እንዲሣተፉ ለማድረግ መታሰቡን ገልፀዋል፡፡ ለወደፊት ለሚከናወነው የክትትልና ግምገማ ሥራ ዕቅድ እንዲዘጋጅ መደረጉንም አብራርተዋል፡፡

51. ከኢንስቲትዩቱ የፕሮጀክቶች ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ መምሪያ ኃላፊ ጋር በተደረገ ቃለ-ምልልስ፣ የፕሮጀክት ሥራ ሂደትን በሚመለከት በየወሩና በየሩብ ዓመቱ ከየፕሮጀክቶቹ ሪፖርት የሚቀርብላቸው መሆኑን፣ እንደአስፈላጊነቱ የመስክ ሥራ እንዲከናወን የሚደረግ መሆኑን፣ በየሩብ ዓመቱም በሥራ አመራር ስብሰባ ላይ ሪፖርት እንደሚቀርብ ገልፀዋል፡፡

52. በመውጫ ስብሰባው ወቅት በስራ ኃላፊዎቹ እንደተገለጸው የክትትልና ግምገማ ስራ ከBPR በፊት በተጠናከረ መልኩ የማይሰራበት ሁኔታ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን ሁኔታው የተሻሻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

53. የፕሮጀክቶች ዕቅድ፣ ክትትልና ግምገማ መምሪያ የፕሮጀክቶችን ሥራ አፈፃፀም (Performance) ለመከታተልና ለመገምገም ዕቅድ ማዘጋጀትና ተፈፃሚ ማድረግ ሲገባ ተግባራዊ አለመደረጉ አግባብነት ያለው አሠራር ሆኖ አልተገኘም፡፡ የምርምር ሥራውን የሚያከናውነው የጅማ ማዕከልም ዕቅድ አለማዘጋጀቱና በቋሚ የጊዜ ገደብ የክትትልና ግምገማ ሥራውን አለማከናወኑ ተገቢነት ያለው አሠራር ሆኖ አልተገኘም፡፡

54. አንድ ፕሮጀክት ሲቀረጽ በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት ውስንና በቅድሚያ የተለዩ፣ እያንዳንዱ ሥራ በምን ያህል ጊዜ መከናወን እና መጠናቀቅ እንዳለበት፣ አጠቃላይ የፕሮጀክቱ የሥራ ዘመን፣ የገንዘብ መጠንና ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልግ የሰው ኃይል ወዘተ… ወሰን የተደረገለት እና በዝርዝር የሚገለጽ እንደመሆኑ መጠን ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ፣ ወጪና ሀብት በብቃት መከናወን እና ስኬታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢው የክትትልና የግምገማ

ሥርዓት ሊዘረጋለትና ሊከናወን ይገባል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው በየደረጃው የተከናወነው የፕሮጀክቱ ሥራ በተያዘለት ጊዜ፣ ወጪና በተፈቀደለት ሀብት መሠረት ጥራትና ብቃት ያለው ሥራ ስለመከናወኑ፣ የመፍትሄ እርምጃ ለመውሰድና ለውሣኔ እንዲረዳ ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ክትትልና ግምገማ ተደርጎ ውጤቱን ለሥራ አመራር የማቅረብ ሥራ በተገቢው ሁኔታ ያልተከናወነ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

55. የፕሮጀክቱን ሁለንተናዊ ሂደት እና በየደረጃው መኖር ስላለበት የሥራ ውጤት፣ የሥራው አካሄድ በፕሮጀክቱ የተያዘው ዓላማ ስኬታማ እንዲሆን በሚያስችል መልኩ አቅጣጫ የያዘ ስለመሆኑ ባለድርሻ አካላትን በማሣተፍ የግምገማ ሥራ (Evaluation) ቢያንስ በፕሮጀክቱ አጋማሽ ወቅት (Mid-term) መከናወንና ስለውጤቱም ሪፖርት መዘጋጀት ሲገባው ይህም ተግባራዊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

56. በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቱ በተያዘለት የጊዜ ገደብ /1994-1998/ እንዳይጠናቀቅ አስተዋፅኦ እንዳደረገ፣ ላለመጠናቀቁም ምክንያቶቹ በትክክል እንዲለዩ ላለመደረጉ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ይታመናል፡፡

57. የክትትልና ግምገማ ሥራው ዕቅድ ተዘጋጅቶለትና በተገቢው መንገድ እንዲከናወን አለመደረጉ በፕሮጀክቱ የሥራ ሂደት ያጋጥማሉ ተብለው በቅድሚያ የተለዩ ሥጋቶች (Risks) የመከላከያ ወይም በፍጥነት የማስተካከያ እርምጃ የመውሰጃ ዘዴዎች ተግባራዊ ለማድረግ፣ በየጊዜው የማሻሻያ እርምጃዎች ለመውሰድና ዳግመኛ ችግሮች እንዳይከሰቱ ለማድረግ፣ ውጤታማ የሥራ ተሞክሮዎችን ለመለየትና ለወደፊት ለሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ልምድ መቅሰሚያ እና ድርጅታዊ አቋምን ለማጠናከር እንቅፋት እንደሚሆን ይታወቃል፡፡ ይህም በበኩሉ ለሀገር ሀብት መባከን አስተዋጽኦ የሚዳርግና ተጠያቂነት ለማጠናከር እንቅፋት እንደሚሆን ይታወቃል፡፡

## <u>በግብርና ምርምር ስራ ላይ ከተሰማሩ የክልል መ/ቤቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ</u>

58. በፌዴራልና በክልል የምርምር ማዕከላት በሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አላስፈላጊ የሆነ የስራ ድግግሞሽና የሀብት መባከን እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክት ግምገማ ስርዓት አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

59. በፌዴራልና በክልል የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አላስፈላጊ የሆነ የስራ ድግግሞሽና የሐብት መባከን እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችል የፕሮጀክት ግምገማ ስርዓት አግባብ ካላቸው የክልል አካላት ጋር በመተባበር መዘርጋት ለኢንስቲትዩቱ የተሰጠ የስራ ኃላፊነት ቢሆንም ወጥነት ያለው ስራ ለመስራት የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

60. ይህንንም በተመለከተ ከኢንስቲትዩቱ የሰብል ምርምር ዳይሬክተር ጋር በተደረገ ቃለ ምልልስ ለማወቅ እንደተቻለው ግንኙነቱ በሰዎች መልካም ፈቃደኝነት ላይ የተወሰነ ሆኖ በዓመት አንድ ጊዜ ከክልል ምርምር ማዕከላት ጋር ውይይት የሚደረግበት አሰራር መኖሩን፣ የዚህ ዓይነቱን አሰራር ለማስቀረትና ወጥነት ያለው ስርዓት ለመመስረት ብሔራዊ የግብርና ምርምር ማስተባበር ሰነድ እየተዘጋጀ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ እንደተቻለው በፌደራልና በክልል ግብርና ምርምር ተቋማት እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መካከል በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የግንኙነት ስርዓት ባለመዘርጋቱ ችግር መፈጠሩን ነው፡፡ ሁኔታው የስራ መደራረብና የሀብት መባከን ለመቀነስ፣ የልምድ ልውውጥ ለማድረግም ሆነ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት በግብርናው ዘርፍ ያለውን ምርምር ውጤታማ ለማድረግ አዳጋች መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡ በፌዴራልና በክልል የሚሰሩ የግብርና ምርምር ስራዎች ውጤታቸው አገሪቷን በግብርናው ዘርፍ የበለጠ ለማሳደግ እና ዘርፉ ለኢኮኖሚው እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ለማብቃት፣ በመሆኑ የስራ ድግግሞሽ መኖሩ የሀብት ብክነት የሚያስከትል ይሆናል፡፡

61. በመውጫ ስብሰባው ወቅት በኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች እንደተገለጸው የቅንጅታዊ አሠራር ሥርዐት አለመኖር በኢንስቲትዮቱ BPR ከመሰራቱ በፊት የነበረ ሁኔታ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን በተጠናከረ መልኩ የተጀመረ መሆኑን ገልፀዋል።

## <u>በምርምር ስራው ላይ ያሉ ባለድርሻዎችን የመለየት ስራን በተመለከተ</u>

62. በእያንዳንዱ የምርምር ፕሮጀክት ተጠቃሚና ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት በቅድሚያ የሚለዩበት የትንተና ስራ (Stakeholders Analysis) እንዲከናወን መደረግ ይኖርበታል፡፡

63. በኦዲቱ ወቅት ተጠቃሚና ተሳታፊ የሆኑ አካላት የሚለዩበት ስራ ተሰርቶ የተገኘ መሆኑን እና በBPR ዶክመንቱም ተጠቃሚዎች በዝርዝር የተለዩበት ሁኔታ ያለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

64. በምርምር ስራው ላይ ተጠቃሚና ተሳታፊ የሆኑ አካላትን መረጃ መያዝና የትንተና ስራ መስራት እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በዘርፉ የሚኖረውን ተሳትፎ ለማወቅና የስራ ግንኙነት ለማድረግ እንዲሁም የሚዘጋጀውን እቅድ የተሟላ የሚያደርግ በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው አሰራር ነው፡፡

# ክፍል ሦስት

## <u>የማሻሻያ ሐሳቦች</u>

65. የምርምር ፕሮጀክት ሥራዎችን ወጥነት ባለው መንገድ በሚፈለገው ጥራት ደረጃ በቁጠባና በብቃት ለማከናወን የሚያስችል የሥራ መመሪያ ሊዘጋጅና ሥራ ላይ እንዲውል ሊደረግ ይገባል፡፡

66. የምርምር ሥራ ፕሮጀክቶችን ሥራ በየደረጃው ለማከናወን፣ ለመከታተል፣ ለመገምገምና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስትራቴጂክ ዕቅድ እንዲዘጋጅ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህ መሆኑ የፕሮጀክት ሥራዎች በቅድሚያ በተነደፈላቸው ስልት ወይም ዘዴ እንዲከናወኑ፣ በተያዘላቸው ዕቅድ መሠረት እንዲጠናቀቁ እና የተነደፉበትን ዓላማ እንዲያሳኩ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

67. ማንኛውም የምርምር ፕሮጀክት ሥራ የሚፈለገውን ውጤት በሚፈለገው ወቅት ለማስገኘት እንዲያስችል በተያዘለት ጊዜ ሊጀመር፣ በየደረጃውም ሊከናወን እና ሊጠናቀቅ ይገባል፡፡ ሥራው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ካልተጠናቀቀ ሊጠናቀቅ ያልቻለበት ምክንያት ተለይቶ በወቅቱ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

68. ማንኛውም ፕሮጀክት ኦዲት ሊደርግ፣ በኦዲት ውጤት ላይ በመመርኮዝ የሚሰጡ የማሻሻያ ሐሣቦችም ተግባራዊ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በቡና ምርምር ፕሮጀክት ላይ በውጭ ኦዲተሮች የተለዩት ግኝቶችና የተሰጡት የማሻሻያ ሐሳቦች ተፈፃሚ ስለመሆናቸው የኢንስቲትዩቱ የውስጥ ኦዲት በመከታተል ውጤቱን ለበላይ ኃላፊ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

69. የምርምር ፕሮጀክቶች በዕቅድ የያዙዋቸው ዝርዝር ተግባራት በየደረጃው በትክክል እየተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ እና አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የክትትል እና የግምገማ ሥራ እንዲከናወን መደረግ ይኖርበታል፡፡

70. በፌዴራልና በክልል የግብርና ምርምር ማዕከላት የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች መካከል አላስፈላጊ የሥራ ድግግሞሽ እና የሀብት መባከን

እንዳይኖር አግባብ ያላቸውን ባለድርሻ አካላት የሚያሳትፍ የፕሮጀክት ዕቅድና ግምገማ (Evaluation) ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

71. በፕሮጀክቶች ላይ በየጊዜው የሚከናወነው የክትትልና የግምገማ ሥራ ውጤት ሪፖርት እየተዘጋጀ ለበላይ ኃላፊ ሊቀርብ ይገባል፡፡

72. በኢንስቲትዩቱ እና በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት /ከብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የግብርና ምርምር ማዕከላት፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወዘተ…/ መካከል በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል የግንኙነት ሥርዐት እንዲዘረጋ መደረግ ይኖርበታል፡፡

73. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በኢንስቲትዩቱ እና በምርምር ማዕከላቱ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡